የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሠላሳ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፲
አዲስ አበባ ታህሳስ ፪ ቀን ፪ሺ.፲፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31th Year No 10
ADDIS ABABA, 11th December, 2024

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ.፫፻፵፯/፪ሺ.፲፯

ለፓሎች-ማታንግ-ማይውት-ፓጋክ መንገድ ስራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ለደቡብ ሱዳን ሪፐብሊክ ለማቅረብ የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ …………………………………………………ገጽ፲፯ሺ.፬፻፲

**Content**

Proclamation No. 1347/2024

Loan Agreement for the Republic of South Sudan for financing the Paloch-Mathiang-Maiwut-Pagak Road Project Ratification Proclamation………….. ……………………………………..Page 17410

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ.፫፻፵፯/፪ሺ.፲፯

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በደቡብ ሱዳን ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገዉን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ**

የፓሎች-ማታንግ-ማይውት-ፓጋክ መንገድ ስራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፯፻፴፰ ሚሊዮን ፪፻፷፬ሺ.፩፻፶ ከ፺፬ ሳንቲም የአሜሪካን ዶላር (ሰባት መቶ ሰላሳ ስምንት ሚሊዮን ሁለት መቶ ስልሳ አራት ሺህ አንድ መቶ ሃምሳ ከ፺፬ ሳንቲም የአሜሪካን ዶላር) ለማቅረብ የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በደቡብ ሱዳን ሪፐብሊክ መካከል እ.ኤ.አ ሜይ ፲፰ ቀን ፪ሺ.፳፫ በጁባ የተፈረመ በመሆኑ፤

## PROCLAMATION No. 1347/2024

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE REPUBLIC OF SOUTH SUDAN**

**WHEREAS**, the Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of South Sudan stipulating that the Federal Democratic Republic of Ethiopia provide to the Republic of South Sudan a Loan amount of Seven Hundreds Thirty Eight Million Two Hundreds Sixty Four Thousands One Hundred Fifty and Ninety four cents United States Dollars (USD 738,264,150.94) for financing Paloch-Mathiang-Maiwut- Pagak Road Project, was signed in Juba on 18th day of May 2023;

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥቅምት ፳፮ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም በአካሄደዉ ፬ኛ መደበኛ ስብሰባ ያጸደቀዉ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሳዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "ለፓሎች-ማታንግ-ማይውት-ፓጋክ መንገድ ስራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ለደቡብ ሱዳን ሪፐብሊክ ለማቅረብ የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፵፯/፪ሺ፲፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. <u>የስምምነቱ መጽደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በደቡብ ሱዳን ሪፐብሊክ መካከል እ.ኤ.አ ሜይ ፲፰ ቀን ፪ሺ፳፫ በጁባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ፀድቋል፡፡

፫. <u>የገንዘብ ሚኒስቴር ስልጣን</u>

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የሚቀርበውን ፯፻፴፰ ሚሊዮን ፪፻፷፬ሺ፩፻፶ ከ፺፬ ሳንቲም የአሜሪካን ዶላር (ሰባት መቶ ሰላሳ ስምንት ሚሊዮን ሁለት መቶ ስልሳ አራት ሺህ አንድ መቶ ሃምሳ ከ፺፬ ሳንቲም የአሜሪካን ዶላር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**WHEREAS**, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Loan Agreement at its 4th regular session held on 5th day of November 2024;

**NOW, THERFORE**, in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Constitution, it is hereby proclaimed as follows.

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "Loan Agreement for the Republic of South Sudan for financing the Paloch-Mathiang-Maiwut-Pagak Road Project Ratification Proclamation No.1347/2024".

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan Agreement signed in Juba on 18th day of May 2023 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of South Sudan is hereby ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Finance</u>**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of Seven Hundreds Thirty Eight Million Two Hundreds Sixty Four Thousands One Hundred Fifty and Ninety four cents United States Dollars (USD 738,264,150.94) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**፬. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ ፪ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም**

**ታዬ አጽቀሥላሴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 11th Day of December, 2024**

**TAYE ATSKE SELASSIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**